# ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምባቸውን ዕቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የካቲት/2002 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት የሚፈፀምባቸውን እቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥ 41/2002

ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለመፈፀም የሚችሉትን እቃዎች ዓይነት ለመዘርዘርና ከጉምሩክ ቁጥጥር የሚለቀቁበትን ሥርዓት በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፣

እቃዎችን ከጉምሩክ ቁጥጥር ከመልቀቅ አሰራር ጋር ተያይዞ ሊፈጠር የሚችለውን ተገቢ ያልሆነ የአገልግሎት መጓተቱ ለማስተካከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 15(4) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምባቸውን እቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 41/2002 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-

1. "እቃ" ማለት በቀላሉ የሚቀጣጠል፣ የሚተን፣ የሚበላሽ፣ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በአስቸኳይ የሚፈለግ ሲሆን በመጋዘን ውስጥ በመቆየት በንብረት ወይም በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ማንኛውንም እቃ ይጨምራል፡፡

2. "የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት" ማለት ወደ አገር የሚገባ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ወይም ተላላፊ እቃ የጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውም የጉምሩክ አፈፃፀም ሂደት ነው፡፡

3. "የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ገቢና ወጪ እቃዎች ወይም ተላላፊ እቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚቆዩበት በባለሥልጣኑ ወይም ከባለሥልጣኑ ፈቃድ በተሰጠው ሰው የተቋቋመ ማናቸውም የእቃ ማከማቻ ቦታ ነው፡፡

4. "እቃን መልቀቅ" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያለ እቃ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በባለሥልጣኑ የሚለቀቅበት ሥርዓት ነው፡፡

5. "አስመጪ" ማለት እቃን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው ነው፡፡

6. "ላኪ" ማለት እቃን ወደ ውጭ አገር የሚልክ ሰው ነው፡፡

7. "የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አስፈፃሚ" ማለት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን የማስፈፀም ተግባር ለማከናወን የሚያስችል የብቃትና የሙያ ማረጋገጫ የተሰጠው የአስመጪ ወይም የላኪ ወኪል ነው፡፡

8. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

9. "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

10. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

3. ***የመመሪያው ተፈፃሚነት***

*ይህ መመሪያ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለማጠናቀቅ ወደ ጉምሩክ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡*

## ክፍል ሁለት
## ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ስለሚለቀቁ እቃዎች

4. ***ዓይነት***

*የሚከተሉት እቃዎች ወደ አገር ከገባ በኋላ ወይም ሳይገባ አስመጪው ወይም ላኪው ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አስፈፃሚው በሚያቀርበው ማመልከቻ መሰረት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት እንዲፈፀም የገቢ ወይም የወጪ እቃዎች አወጣጥ ቡድን ሊፈቅድ ይችላል፡፡*

ሀ/ መድሐኒቶች፣

ለ/ በቀላሉ የሚቀጣጠሉ እቃዎች፣

ሐ/ ጨረር አመንጪ መሣሪያዎች፣

መ/ ዘር እና ችግኞች፣

ሠ/ በሕይወት ያሉ እንስሳት እና ጫጩት የመሳሰሉት፣

ረ/ ለምርመራና ለላብራቶሪ የሚውሉ ነፍሳት ወይም ዕፅዋት፣

ሰ/ ለወጪ እቃዎች ግብዓት የሚሆኑ እቃዎች

ሸ/ በመትነን አካባቢን የሚበክሉ ኬሚካሎች፣

ቀ/ ወቅታዊ የሆኑ መጽሔቶችና ጋዜጦች፣

በ/ ምግቦች፣ ፍራፍሬዎች፣

ተ/ ወጪ እቃዎች፣

ቸ/ ለአንድ ተቋም መደበኛ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ በአፋጣኝ ካልገቡ ሥራው ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ እቃዎችና መለዋወጫዎች፣

ነ/ ሌሎች ባለሥልጣኑ በሰርኩላር የሚያስተላልፋቸው እቃዎች፡፡

5. <u>ስለማመልከቻ አቀራረብ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ላይ የተዘረዘሩት እቃዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ከጉምሩክ ቁጥጥር እንዲለቀቁ የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን ዕቃው ወደ አገር ከመግባቱ በፊት ወይም በገባ በ8 የሥራ ሰዓት ውስጥ በፁሑፍ እና አግባብ ያላቸውን ሰነዶች በማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6. <u>ማመልከቻን ስለመመርመር</u>

1. አቤቱታ የቀረበለት የገቢ ወይም የወጪ እቃዎች ቡድን ማመልከቻውንና ሰነዶችን መርምሮ እስከ አንድ ሰዓት ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

2. ሰነዶቹ ወይም ዕቃዎቹ ሲመረመር ወይም ሲፈተሽ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ሥር ከተዘረዘሩት መካከል ያልሆነ እንደሆነ በመደበኛው ሥነ-ሥርዓት እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

7. <u>ስለኃላፊነት</u>

ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሰራተኛ በዚህ መመሪያ እና በአዋጁ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 90 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

8. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ተፈርሞ ከወጣበት እለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ______________ቀን 2002 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር